## ወንጀልን ለማጋለጥ የተጋራ የመረጃ አገልግሎት መታወቂያ

## 2026-050-FB-UA

ቦርዱ፣ ወንጀልን እና ግጭትን ለማጋለጥ በሚደረግ ጥረት የግል መለያ መረጃዎችን የያዙ እና ሃሰተኛ ሊሆኑ የሚችሉ የመንግስት መታወቂያዎችን ማጋራትን የሚመለከቱ የሜታ ፖሊሲዎችን ለመገምገም የኢትዮጵያ መረጃ አገልግሎት መታወቂያ በአንድ አክቲቪስት መጋራቱን የሚመለከት ጉዳይ መርጧል። ይህ ጉዳይ ሰዎች የሕግ አስከባሪዎችን ወይም የሕግ አስከባሪ ነን ባዮችን ድርጊት አስመልክቶ ስጋት ሲያድርባቸው፣ የማህበረሰባቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ምን ዓይነት መረጃዎችን ማጋራት እንዳለባቸው ለመዳሰስ ጥሩ አጋጣሚ ይሰጣል።

በ2026፣ የኢትዮጵያ ፖለቲከኛና አክቲቪስት ጃዋር ሞሃመድ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ በፌስቡክ ገጹ ላይ አንድ ልጥፍ አጋርቷል። ጃዋር በጽሑፉ ላይ “120” የተባለ የተደራጀ የወንጀል ቡድን፣ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት (NISS) መታወቂያን በመጠቀም በኦሮሚያ ክልል ዜጎችን እያሰቃየ እና እየዘረፈ መሆኑን እንደሰማ ይገልጻል። የቡድኑን መሪ እና በዝርፊያው ውስጥ ይሳተፋሉ የሚላቸውን ሁለት ግለሰቦች ስም የጠቀሰ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል አንደኛው፣ የቀድሞ የፖሊስ አባል ሲሆን አሁን ለቡድኑ እንደሚሰራ ይናገራል። እንደ “ማስረጃ” ልጥፉ ስም፣ የስራ ድርሻ፣ ፎቶግራፍ እና የስልክ ቁጥር የያዘ የኢትዮጵያ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት (NISS) መታወቂያ ምስልን፣ እንዲሁም የሁለት ወንዶች ፎቶዎችን አካቷል። በፎቶዎቹ ውስጥ ካሉት ወንዶች አንዱ በመታወቂያ ካርዱ ላይ ከሚታየው ሰው ጋር ይመሳሰላል፣ ሌላኛው ደግሞ የወታደር መለዮ የሚመስል አድርጓል። ይህ ይዘት በተለጠፈበት ወቅት ስለ “120” ቡድን ሰፊ ውንጀላዎች እና የሚዲያ ዘገባዎች ይነገሩ ነበር። የጃዋር ሞሀመድ ገጽ ከ3.4 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች ያሉት ሲሆን፣ ልጥፉ ወደ 400 የሚጠጉ ኮመንቶችን አግኝቷል።

ከተለጠፈ ከሶስት ቀናት በኋላ፣ ሜታ ለሰኔ 2026 ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ ካደረገው ዝግጅት አካል አድርጎ ያቋቋመው ቡድን፣ ልጥፉን በመለየት ለባለሙያዎች ግምገማ መርቷል። ሜታ የግል መለያ መረጃዎችን (PII) ማጋራትን እንዲሁም የሕግ አስከባሪ፣ የወታደራዊ ወይም የደህንነት ሠራተኞችን የመንግስት መታወቂያዎች ማጋራትን በግልጽ የሚከለክለውን የግል ሚስጥራዊነት ጥሰት (Privacy Violations) ፖሊሲ በመተላለፉ ምክንያት በቀጣዩ ቀን ልጥፉን አውርዶታል። ሆኖም፣ የመታወቂያው ፎቶ እውነተኛ መሆኑ እና አለመሆኑ ግልጽ ባለመሆኑ ምክንያት ምንም ዓይነት የቅጣት እርምጃ (strike ) ወይም የአጠቃቅም ገደብ አልተጣለብትም።

የጃዋር ሞሀመድ የይግባኝ ጥያቄ በሰው ለሚደረግ ግምገማ ቅድሚያ ባለማግኘቱ ምክንያት ተዘግቷል። ጃዋር ሞሀመድ ውሳኔውን ለክትትል ቦርዱ (Oversight Board) ይግባኝ በማለት፣ የወንጀል ቡድኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት (NISS) ባለስልጣናትን ማንነት፣ ሃሰተኛ መታወቂያዎችን በመጠቀም ዜጎችን እንደሚያስር፣ በማስፈራራትም ገንዘብ እንደሚዘርፍ ከዚያም የባሰ በደል እንደሚፈጽም ሰምቶ እንደነበር ገልጿል። እሱ ባደረገው

ምርመራ መሰረት፣ ከሀሰተኛ መታወቂያዎች ኮፒ አንዱን እንዳገኘ እና በመታወቂያው ላይ ያለው ስም በፎቶው ላይ ከሚታየው ሰው ጋር እንደማይመሳሰል፣ እንዲሁም መታወቂያው በህጋዊ መንገድ ከባለስልጣኑ አካል እንዳልተሰጠ አግባብነት ካለው የመንግስት አካል ማረጋገጡን አስረድቷል። የመታወቂያውን ምስል ዜጎችን ለማስጠንቀቅ እና ሰዎችን ከመጭበርበር እና ከዝርፊያም ለመታደግ ሲል ለህዝብ ማስጠንቀቂያ ይሆን ዘንድ እንደለጠፈው አብራርቷል። ልጥፉ የማንንም ሰው ግላዊነት ለመጣስ የታለመ ሳይሆን፣ ይልቁኑ የደህንነት ባለስልጣናት ነን በማለት ለማጭበርበር ሀሰተኛ መታወቂያዎችን የሚጠቀሙ ግለሰቦችን ለማጋለጥ የተዘጋጀ መሆኑን አክሎ ገልጿል። ተጠቃሚዎች ለሜታ ይግባኝ ሲያቀርቡ ምክንያታቸውን ማስረዳት ወይም ኩባንያው ሊያጤናቸው የሚችሉ ተዛማጅ ሐሳቦችንና ሁኔታዎችን ማቅረብ እንደማይችሉ ቦርዱ ያስተውላል።

ቦርዱ ይህን ጉዳይ መምረጡን ተከትሎ፣ ሜታ ውሳኔውን እንደገና መርምሮ ይዘቱ የግል ሚስጥራዊነት ፖሊሲን እንደሚተላለፍ አጽንቷል። ሆኖም፣ ጥሰቱ የመታወቂያ ካርዱን በማጋራት ብቻ የተወሰነ በመሆኑ፣ ኩባንያው የመታወቂያውን ምስል ሳይጨምር የቀረውን የልጥፍ ክፍል መመለስ ችሏል። ኩባንያው አክሎ በሰጠው ማብራሪያ፣ ፖሊሲው ተጠቃሚዎች የግል መለያ መረጃዎችን (PII) በማጥፋት መታወቂዉን እንዳይለጥፉ፣ ወይም የግል መለያ መረጃዎቹ የማይታዩበትን የመታወቂያውን የተወሰነ ክፍል ብቻ እንዳይለጥፉ አያግደውም።

ቦርዱ የሚከተሉትን ነጥቦች የሚዳስሱ የህዝብ አስተያየቶችን መቀበል ይፈልጋል፦

- የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በአንድ በኩል ስለ ሙሰኛ የሕግ አስከባሪዎች እና የሕግ አስከባሪ ነን ስለሚሉ ማጭበርበሮች መረጃዎችን ከሚያጋሩ ሰዎች፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕጋዊ የሕግ አስከባሪ ሠራተኞችን ከመጠበቅ አንፃር የሚነሱ ተቃራኒ ፍላጎቶችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው።
- በተለይም ቀውስ እና ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች፣ የሜታ ፖሊሲዎች ተጠቃሚዎች በወንጀል ድርጊቶች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ከማስቻል እና በእነዚህ ድርጊቶች ውስጥ ተሳትፈዋል ከተባሉ ግለሰቦች ማንነት እና የግል መረጃ ጥበቃ ጋር ትክክለኛውን ሚዛን የጠበቁ መሆኑን አለመሆኑን።
- የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በኢትዮጵያ ወይም በሌሎች በቂ ውክልና በማይገኙባቸው ቋንቋዎች፣ በተለይም ስለ ወንጀል፣ ማጭበርበር እና የመሳሰሉት የህዝብ ጥቅም ጉዳዮች መረጃዎችን በማጋራት ረገድ ይዘቶችን በመገምገም ረገድ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ።
- የሰው መብት ተሟጋቾች እና ጋዜጠኞች የሚያጋሯቸውን ይዘቶች በጥልቀት እና በዝርዝር በመገምገም ረገድ፣ በተለይም በአለም አቀፍ አብላጫ ክልሎች ውስጥ ባሉ ምርጫዎች ወይም ቀውሶች ወቅት፣ እንደ ክሮስ ቼክ (cross-check) ያሉ የስህተት መከላከያ ስርዓቶች ያላቸው ሚና እና ድክመቶች።
- የይዘት ማጣራት ውሳኔዎች ውጤታማ ግምገማ እንዲኖር ለማድረግ የይግባኝ እና የፍትሃዊ ሂደት (due process) ሚና፤ ተጠቃሚዎች በይግባኛቸው ላይ ተጨማሪ ሃሳብ እንዲሰጡ ከኢንዱስትሪው አጠቃላይ ልምዶች የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ጨምሮ።

ቦርዱ ውሳኔዎቹን በሚሰጥበት ጊዜ ለሜታ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦችን ማቅረብ ይችላል። ምክረ-ሀሳቦቹ አስገዳጅ ባይሆኑም፣ ሜታ በ60 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። በመሆኑም ቦርዱ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምክረ ሀሳቦች የሚያቀርቡ የህዝብ አስተያየቶችን በደስታ ይቀበላል።